رئاسة الشؤون الدينية
بالمسجد الحرام والمسجد النبوي

# የዑምራ አፈፃፀም ሁኔታ

## ከተመረጡ ዱዓዎች ጋር

የቃሲደል ሀረመይን አሽ-ሸሪፈይን ህትመት

مطبوعات قاصد الحرمين الشريفين

برنامج قاصد الحرمين

رئاسة الشؤون الدينية
بالمسجد الحرام والمسجد النبوي

برنامج قاصد الحرمين

# የዑምራ አፈፃፀም ሁኔታ

## ከተመረጡ ዱዓዎች ጋር

የቃሲደል ሀረመይን አሽ-ሸሪፈይን ህትመት

مطبوعات قاصد الحرمين الشريفين

ⓒ رئاسة الشؤون الدينية بالمسجد الحرام والمسجد النبوي، ١٤٤٦هـ

رئاسة الشؤون الدينية بالمسجد الحرام والمسجد النبوي
صفة العمرة باللغة الأمهرية./رئاسة الشؤون الدينية بالمسجد الحرام والمسجد
النبوي - ط١. .- مكة المكرمة، ١٤٤٦هـ
٣٢ص، ١٤×٢١سم
رقم الإيداع: ١٤٤٦/١٤١٤٨
ردمك: ٥-٤٥-٨٥٠٦-٦٠٣-٩٧٨

የቃሲደል ሀረመይን አሽ-ሸሪፈይን ህትመት

የመጀመሪያው ዕትም
١٤٤٦هـ/٢٠٢٥م

بسم الله الرحمن الرحيم

## የአስተዳደሩ መግቢያ

ምስጋና የሚገባው ለአላህ ነው ፣ የአላህ ሰላም እና ውዳሴ በአላህ መልክተኛ ላይ፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸው እና በተከተሉት ላይ ይሁን። ከዚህም በመቀጠል:-

አላህ የተከበረውን ቤት (ካዕባ) ለሙስሊሞች ልቦች እና አካላት የሚሰበሰቡበት አቅጣጫ አድርጎታል፣ ለዓለማትም መመሪያ፣ እንዲሁም ደህንነቱ የተጠበቀ ክቡር አድርጎታል። የሰዎች መልካም ኑሮ እና መመለሻቸው እሱን በማላቅ እውን ይሆናል።

በየአመቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ተስፋዎቻቸውን፣ ስሜቶቻቸውን እና ምኞቶቻቸውን ይዘው ወደ ተከበረው አገር ይመጣሉ፤ እንዲሁም ስለ ሃይማኖታቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው፤በአምልኮታቸው እና በንግድ ልውውጦቻቸው ግልፅ ያልሆነላቸውን ጥያቄዎችን ያነሳሉ።

ከዚህ አንጻር የተከበረውን መስጂድ፣ ነዋሪዎቹን እና ወደ እሱ የሚመጡትን ማክበር ግዴታ እና ታላቅ ኃላፊነት ነው። “በመስጂደል ሀራም እና በመስጂድ አንነበዊ የሀይማኖታዊ ጉዳዮች አመራር” ይህንን ኃላፊነት በሙሉ መልኩ በማከናወን ላይ ይገኛል።

ይህ “የቃሲደል ሀረመይን አሽ-ሸሪፈይን ህትመት” ፕሮጀክት የዚህ በረከት ያደረባት አገር ሰዎች እና የተከበረውን ቤት አገልግሎት ላይ የቆሙ ሰራተኞች ለአላህ እንግዶች (ወፍድ አል-ረሕማን) ያላቸውን እውነተኛ ስሜት የሚገልፁበት ነው፣ እንዲሁም ጎብኚው ከእሱ ጋር የሚወስደው እና ወደ አገሩ ሲመለስ የሚኮራበት ውድ ስጦታ ነው።

“በመስጂደል ሀራም እና በመስጂድ አንነበዊ የሀይማኖታዊ ጉዳዮች አመራር” የአላህ እንግዶች ለሆኑት ወንድሞቻችን ይህንን መመሪያ መጽሐፍ በማቅረብ ላይ ሲሆን፣ ይህም የዑምራ ሥራዎችን፣ ግዴታዎችን፣ ሱናዎችን፣ የኢህራም ክልከላዎችን እና የተመረጡ ዱዓዎችን ያቀፈ ነው፤ ሙስሊሙም በዑምራው ጊዜ በእዚህ መተግበር አለበት። እኛ ከሙስሊም ወንድሞቻችን ሃይማኖታቸውን እንዲገነዘቡ፤ የተከበረውን ቤት ጉብኝትን ያገራላቸውን እና ሥርዓቱን በሙሉ እርጋታ እና በቀላሉ እንዲፈፅሙ ያደረጋቸውን ጌታቸውን አላህን እንዲያመሰግኑ እንመኛለን።

አላህ ከእኛም ከእናንተም መልካም ስራዎችን ይቀበል። ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ አላህ ይድረስ። አላህ በነቢያችን ሙሀመድ፣ በቤተሰቦቻቸው እና በባልደረቦቻቸው ላይ ሰላምና ውዳሴን ያድርስ።"

በመስጂደል ሀራም እና በመስጂደ አንነበዊ የሀይማኖታዊ
ጉዳዮች አመራር

# መግቢያ

ምስጋና የሚገባው ለአላህ ነው ፤ እናመሰግነዋለን፤ እርዳታውን እንፈልጋለን፤ ምህረትን እንጠይቃለን፤ ከነፍሶቻችን ክፉ ነገሮችና ከሥራዎቻችን መጥፎ ነገሮች በአላህ እንጠበቃለን፤ አላህ የመራውን ሰው ማንም ሊያጠመው አይችልም፤ እርሱ ያጠመመውን ማንም ሊመራው አይችልም፤ ከአላህ ሌላ በሀቅ የሚመለክ አምላክ እንደሌለ፣ ተጋሪ የሌለውና ብቸኛ እንድሆነ እመሰክራለሁ፤ ሙሃመድም (የአላህ ሰላም እና ውዳሴ በሳቸው ላይ ይሁን) ባርያውና መልእክተኛው እንደሆኑ እመሰክራለው። ከዚህ በመቀጠል፡-

በ«በመስጂደል ሃራም እና በመስጂደ አንነበዊይ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች አመራር» የጉዞ ልምድን ለማሳደግ ባላቸው ቁርጠኝነት፣ እንዲሁም በመልካም ነገር፣ በአላህ ፍራቻ ላይ በመተባበር እና ዕውቀትን ለማሰራጨት፣ ይህንን ፅሁፍ ለመልቀቅ ተነሳስተዋል፤ ይህም ለጎብኚዎች እና ለዑምራ አድራጊዎች በቁርአን፣ በሱና፣ እና በዕውቀት ባለቤቶች ንግግር መሠረት ይህን ስነስርዓት ለመፈጸም የሚረዳ ይሆናል። ይህ ትንሽ መልእክት ሚመስል፣ ነገር ግን በዑምራ ስነስርዓት እና ሕጎች ላይ በጣም ጠቃሚ ነው። እናም ዑምራ በየዓመቱ የተፈቀደ ስለሆነ፣ ሕጎቹን እና ስነስርዓቱን ማወቅ የማይቋረጥ እና የሚደጋገም ነው፣ ይህም ከሐጅ ጋር የሚመሳሰል አይደለም፣ ምክንያቱም ሐጅ የተወሰነ ጊዜ እና ወቅት ስላለው። ስለሆነም ይህንን በዑምራ ስነስርዓት አቅርበናል፣ ከዚያም ቁርአን እና በትክክለኛው ሱና ውስጥ የተገኙ ዱዓዎችን አካትተናል።"

አላህ ይህንን ስራ እንዲባርከው፣ ለርሱ ብቻ ጥርት ተደርጎ የተሰራ እንዲሆን፣ ለሙስሊም ባሮቹ ጠቃሚ እንዲሆን እንጠይቀዋለን፤ የአላህ ሰላም እና ውዳሴ በነቢያችን ሙሀመድ ላይ ይሁን።

# ሚቃቶች እና ኢህራም

ሚቃት ማለት ዑምራ ለማድረግ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ኢህራም ማድረግ ያለበት ቦታዎች ናቸው።

ዑምራ ለማድረግ የሚሄድ ሰው ኢህራም ሳያደርግ ማለፍ የማይፈቀድለት ቦታዎች በሀዲስ ላይ ተገልፀዋል ። እነዚህ ሚቃቶች አምስት ናቸው።

ዙል ሁለይፋህ: አሁን ላይ አብያር ዐሊ ተብሎ ይጠራል፤ የመዲና ነዋሪዎች እና ከእነሱ ውጪ በዚህ ቦታ ለሚያልፉ ሚቃት ነው፤ ከመካ (420 ኪ.ሜ) ይርቃል።

አል-ጁህፋህ፡ ከራቢግ ቅርብ የሆነ መንደር ነው፤ የሻም፣ የግብፅ የሞሮኮ ነዋሪዎች እና በዚህ ቦታ ለሚያልፉ ሁሉ ሚቃት ነው፤ ከመካ (186 ኪ.ሜ) ይርቃል። ብዙ ሰዎች ከራብግ ኢህራም ያደርጋሉ።

ቀርንል መናዚል፡ አሁን ላይ አስ-ሰይለል ከቢር ተብሎ ይጠራል፤ የነጅድ፣ የጣይፍ ነዋሪዎች እና በዚህ ቦታ ለሚያልፉ ሁሉ ሚቃት ነው። ከመካ (78 ኪ.ሜ) ይርቃል፤ ዋዲ ማህረም ያዋስነዋል፤ እርሱም በላይኛው ቀርነል መናዚል በአል ሁዳ መንገድ በኩል ያለው ነው፤ ከመካ (75 ኪ.ሜ) ይርቃል።

የለምለም፡ የየመን ነዋሪዎች እና በዚህ ቦታ ለሚያልፉ ሁሉ ሚቃት ነው።ከመካ (120 ኪ.ሜ) ይርቃል።

ዛቱ ዒርቅ፡ አድ-ደሪባህ ተብሎ ይጠራል፤

የኢራቅ ነዋሪዎች እና በዚህ ቦታ ለሚያልፉ ሁሉ ሚቃት ነው። ከመካ (100 ኪ.ሜ) ይርቃል።

ቤቱ ከእነዚህ ሚቃቶች በታች ያለ ሰው፣ ለሐጅ ወይም ለዑምራ ከቤቱ ኢህራም ያደርጋል።ነገር ግን ቤቱ በመካ ውስጥ ያለ ሰው፣ ለዑምራ ወደ አል-ሂል (ከሀረም ክልል ውጪ) መሄድ አለበት። ለሐጅ ግን የመካ ነዋሪዎች ከቤታቸው ወይም ከሚኖሩበት ቦታ ኢህራም ያደርጋሉ።

## ማሳሰቢያ

በአውሮፕላን ለሐጅ ወይም ለዑምራ የሚመጣ ሰው፣ ከሚቃቶች በአንዱ ሲያልፍ አውሮፕላኑ ውስጥ ኢህራም ማድረግ አለበት። ጅዳ አውሮፕላን ማረፊያ እስከሚደርስ መዘግየት የለበትም፣ ምክንያቱም ጅዳ ለነዋሪዎቿ ብቻ የሆነች ሚቃት ናት።

የኢህራም ልብስ ከሌለው ሱሪውን አስቀርቶ ከላይ ያለው ልብሱን አውልቆ በትከሻውና በደረቱ ላይ በማስቀመጥ ኢህራም ያደርጋል፤ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርስህ የኢህራም ልብስ ባገኘ ጊዜ ሱሪውን አውልቆ የኢህራሙን ልብስ ይለብሳል።

ሴት ልጅ ደግሞ ልዩ የኢህራም ልብስ የላትም። በለበሰችው ልብስ አውሮፕላን ውስጥ ኢህራም ታደርጋለች፤ኒቃብ ወይም ቡርቁዕ ወይም ጓንት ካደረገች ታወልቀዋለች፤ በዙሪያዋ አጅነቢ ወንዶች ካሉ ፊቷን በሻሽ(ጉፍታ) ትሸፍነዋለች።

# የዑምራ ማእዘናት ገዴታዎች እና ሱናዎች

የዑምራ ማእዘናት፡

1. ወደ ዑምራ ተግባር ሊገባ ሲል ቀድሞ ማሰብ(መነየት)።

2. ካዕባን መዞር ።

3. በሰፋ እና መርዋ መሃከል መሮጥ።

ከዑምራ ማዕዘናት አንዱን የተወ ሰው ዑምራውን በተደነገገው ሸሪዓዊ ሁኔታ እስካልፈፀመ ድረስ ተቀባይነት የለውም።

የዑምራ ግዴታዎች፡

1. በሚቃት በኩል ለሚያልፍ ከራሱ ከሚያልፍበት ሚቃት ኢህራም ማድረግ፤ ቤቱ ከሚቃት በፊት የሆነ ሰው የሱ ኢህራም ማድረጊያ ከሚነሳበት ቦታ ይሆናል፤ የመካ ነዋሪ የሆነ ሰው ወደ ሒል (ከሀረም ክልል ውጪ) ቦታ ሄዶ ኢህራም ማድረግ ይጠበቅበታል።

2. ፀጉርን መላጨት ወይንም ማሳጠር።

- ከዑምራ ግዴታዎች አንዱን አውቆ እና ሆነብሎ የተወ ሰው ኃጢአተኛ ሲሆን ፊድያ (ቤዛ/መቀጫ) ግዴታ ይሆንበታል። ሳያውቅ የተወ ሰው ፊድያ ብቻ ግዴታ ይሆንበታል።

የዑምራ ሱናዎች(ተወዳጅ ተግባራት)፡

- ከዑምራ ማእዘናት እና ግዴታዎች ውጪ ያሉት እንደ አልኢድጢባዕ (የኢህራም ልብስን በማጣፋት የቀኝ ትከሻን

ግልፅ ማድረግ) እና ረመል (የመጀመሪያዎቹን ሶስት የጠዋፍ ዙር በሶምሶማ መሮጥ) ተግባራት ሱናዎች ናቸው።

- አንድን የሱና ተግባር የተወ ሰው ምንም የለበትም።ነገር ግን የምንዳ ትሩፋት ያመልጠዋል።

## የኢህራም ክልከላዎች፡

የኢህራም ክልከላዎች በሶስት ይከፈላሉ፡

የመጀመሪያው፡ በወንዶች እና በሴቶች ላይ ክልክል የሆኑ ነገሮች፡

1. ሙህሪም የሆነ ሰው የኢህራም ኒያ ካደረገ ቡኃላ ከፀጉሩ እና ከጥፍሩ መንካት አይፈቀድለትም።
2. ሙህሪም የሆነ ሰው ጥሩ መዓዛ ያላቸው አይነቶችን ሁሉ መራቅ አለበት።
3. የእጅ ጓንቶችን መልበስ አይፈቀድም።
4. ሙህሪም የሆነ ሰው ማጨት ፣ለራሱም ሆነ ለሌላ ሰው ኒካህ ማሰር አይፈቀድለትም።
5. ሙህሪም የሆነ ሰው የግብረስጋ ግንኙነትን እና ወደሱ የሚገፋፉ ተግበራት እርም ይሆንበታል።
6. ኢህራም ውስጥ እስካለ ድረስ በየብስ ላይ ያሉ እንስሳትን ከማደን፣ ከማደናበርም ሆነ ለአደን ከመተባበር ራሱን ማጋላጥ የለበትም።

ሁለተኛው፡ ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች ብቻ የተከለከሉ ነገሮች፡

1. የተሰፉ ልብሶችን በተዘጋጀበት መልክ መልበስ አይፈቀድም።
2. እንደ ጥምጣም እና በመሳሰሉት ጭንቅላትን በሚነኩ ነገሮች መሸፈን አይፈቀድም።

ሶስተኛው፡ ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች ብቻ የተከለከሉ ነገሮች፡

1. በኒቃብ፣ በቡርቁዕ እና በመሳሰሉት ፊቷን መሸፈን ለሴት ልጅ አይፈቅደላትም። ይህም ሲሆን በዙሪያዋ አጅነቢ (ለሷ ያልተፈቀዱ) ወንዶች ካሉ በጉፍታ (ሻሽ) ፊቷን መሸፈን ይኖርባታል።

ከነዚህ ክልከላዎች አንዱን የፈፀመ ሰው ብያኔ፡

- እንዚህን ክልከላዎችን በመርሳት ወይም በአለማወቅ ወይም ተገዶ የፈፀመ እንደሆነ ኃጢአተኛ አይሆንም፤ ፊድያህ (ቤዛ/መቀጫ) የለበትም።
- እነዚህን ክልከላዎችን አስፈላጊ ለሆነ ጉዳይ የፈፀመ እንደሆነ ይፈቀድለታል፤ ፊድያም ግዴታ ይሆንበታል።
- እንዚህን ክልከላዎች ያለምክንያት ወይም ሳያስፈልግ የፈፀመ ኃጢአተኛ ይሆናል።ፊድያም ግዴታ ይሆንበታል።

# የኢህራም ክለከላዎች ፊድያ (ቤዛ) ከመክፈል አንፃር በአይነት ሲከፈሉ

- የመጀመሪያው፡ ፀጉርን እና ጥፍርን ማስወገድ፣ ጥሩ መዓዛ ያለውን ነገር መጠቀም፣ ጓንቶችን መልበስ፣ ወንድ ልጅ የተሰፋ ልብስ መልበሱ፣ የራስ ቅሉን መሸፈኑ፣ ሴት ፊቷን መሸፈኗ እና በስሜት መነካካት ከነዚህ ክልከላዎች አንዱን የፈፀመ ከሶስት አንዱን የፊድያ አይነት ክፈል ይባላል።

  ሀ. ሶስት ቀን አከታትሎ ወይም አለያይቶ መፆም።

  ለ. ወይም እንደ ተምር፣ ሩዝ ወይንም የመሳሰሉትን ለስድስት ሚስኪኖች ለእያንዳንዱ ግማሽ ቁና መመገብ።

  ሐ. ወይም በግ ማረድ፤ ከዛም ሀረም ላሉ ሚስኪኖች ይከፋፈላል።

- ሁለተኛው፡ ከኡምራ ግዴታዎች አንዱን የተወ እንደ ከሚቃት ኢህራም ማድረግን የመሰለ የእርድ ፊድያ እንዲያረግ ይገደዳል። እርዱም ከወንድ ወይም ሴት በግ ወይም ፍየል ለኡድሂያ መስፈርት የበቁ መሆን አለበት፤ ስጋውም ሃረም ባሉ ድሆች እንዲከፋፈል ይደረጋል፤ ከስጋውም መብላቱ ክልክል ይሆንበታል።

- ሶስተኛው፡ የግብረስጋ ግንኙነት ፊድያ (ቤዛ)፡ ሰዕይ ከማድረጉ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ ማንኛውም ሰው ዑምራው ይበላሻል፤ ዑምራውን ማጠናቀቅ አለበት፤ ከዛም ማካካስ (ቀዳእ) አለበት፤ የእርድ ፊድያ ግዴታ ይሆንበታል፤ የሚያርደውን ካላገኘ አስር ቀናትን ይፆማል።

ሳዕይ ካደረገ ቡኋላ እና ፀጉሩን ከመላጨቱ ወይም ከማሳጠሩ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ ከሆነ ኡምራው አይበላሽም፤ የእርድ ፊድያ ግዴታ ይሆንበታል፤ የሚያርደውን ካላገኘ አስር ቀናትን ይፆማል።

አራተኛው፡ የአደን ቅጣት፤ ሁለት ሁኔታዎች አሉት፡

- የታደነው አደን እንደ ጋማ ከብት ከሆነ ከሶስት አንዱን እንዲመርጥ ይደረጋል።

ሀ. ያደነውን አምሳያ ማረድ፤ከዛም በሀረም ዙሪያ ላሉ ድሆች እና ችግረኞች ማከፋፈል፤

ለ. ወይንም ያደነውን የሚመሳሰል የዋጋ ተመን አይቶ በሱ ልክ ምግብን ይገዛል፤ ከዛም በሀረም ዙሪያ ላሉ ድሆች እና ችግረኞች ያከፋፍላል።ለእያንዳንዱ ችግረኛ ግማሽ ቁና ምግብ ይሰጣል።

ሐ. ወይንም ከመመገብ ፋንታ በእያንዳንዱ ድሃ ቁጥር የሚያክል ቀናትን ይፆማል።

- የታደነው እንስሳ አምሳያ የሌለው እንደ አንበጣ እና የመሳሰሉት ከሆነ ከሁለት አንዱን እንዲመርጥ ይደረጋል።።

ሀ. የታደነው እንስሳ ምን ያህል ዋጋ ያወጣል ሚለውን ይመለከትና በተመኑ ልክ ምግብን የሚያወጣ ሲሆን ለችግረኞች ያከፋፍላዋል።ለእያንዳንዱ ሚስኪን ግማስ ቁና ይሰጣል።

ለ. ወይንም ከመመገብ ፋንታ በእያንዳንዱ ድሃ ቁጥር የሚያክል ቀናትን ይፆማል።

# የዑምራ አፈፃፀም ሁኔታ

- ዑምራን አስቦ (ኒያ አድርጎ) ወደ ሚቃት በደረሰ ጊዜ፡
- ከኢህራም በፊት ገላውን መታጠብ እና ጥሩ መዓዛን (ሽቶን) መጠቀም ይወደድለታል።
- ወንድ ልጅ ከላይ ፎጣ እና ከስር ሽርጥን ይለብሳል።ሁለቱም ንፁህ እና ነጭ መሆናቸው ይወደዳል።
- ሴት ደግሞ የፈለገችውን ሰውነቷን በሚገባ መልኩ የሚሸፍን ልብስ ለብሳ ኢህራም ማድረጓ ይፈቀድላታል።ነገር ግን ኒቃብ ሆነ ጓንት አትለበስም።
- በልቡ ወደ ኢህራም ተግባር እየገባ እንደሆነ ያስባል።ያሰበውን በምላሱ መናገርን ተደንግጎበታል። “ለበይከ ዑምረተን” ወይንም “አልላሁመ ለበይከ ዑምረተን” ይላል።
- ኢህራም ያደረገ ሰው የዑምራ ስነስርዓት ማከናወን እንደማይችል ቢፈራ (ለምሳሌ በህመም ወይም በጠላት ምክንያት)፣ ኢህራም ሲያደርግ ይህን ማለት ይመረጣል፡ ”ፈኢን ሀበሰኒ ሃቢሱን ፈመሂሊ ሃይሱ ሃበስተኒ።” (አንዳች የሚያግደኝ ነገር ቢፈጠር፣ የምፈታው ባገድከኝ ቦታ ላይ ነው።) የዚህ መስፈርት ጥቅም፡- ኢህራም ያደረገ ሰው ስነስርዓቱን ለማጠናቀቅ የሚያግደው ነገር (ለምሳሌ ህመም ወይም ጠላት) ቢያጋጥመው፣ ሳያጠናቅቅ ከኢህራም መፈታት ይፈቀድለታል፤ እናም ምንም ቅጣት አይኖርበትም።
- ወደ መካ በሚጓዝበት ጊዜ የተልቢያን ዚክር ማብዛት እና ድምፁን ከፍ አድርጎ መደጋገም ይወደድለታል።

- ዑምራ የሚያደርግ ሰው ወደ መስጂደል ሀራም በሚገባበት ጊዜ ሚያደርጋቸው ነገሮች፡

- መስጂደል ሀራም የደረሰ ሰው ወደ ውስጥ በሚገባበት ጊዜ ቀኝ እግሩን ማስቀደም ይወደድለታል “ቢስሚላህ ወሰላቱ ወሰላሙ ዓላ ረሱሊላህ” (በአላህ ስም፤ በመልዕክተኛው ላይ የአላህ ሰላም እና ውዳሴ ይሁን) (ኢብን ማጃህ ዘግበውታል)፤ “አዑዙ ቢላሂል ዐዚም ወቢወጅሂሂል ከሪም ወሱልጣኒሂል ቀዲም ሚነሸይጣኒረጂም” (በተላቀው አላህ ፤ክቡር በሆነው ፊቱ፣ ቀደምት በሆነው ስልጣኑ ከሸይጣን እጠበቃለው) (አቡ ዳዉድ ዘግበውታል)፤ “አላሁመፍታህ ሊ አብዋበ ራህመቲከ” (አላህ ሆይ የእዝነትህን በር ክፈትልኝ) (ሙስሊም ዘግበውታል)።

- ጠዋፍን ለመጀመር ወደ ሀጀረል አስወድ (ጥቁር ድንጋይ) ይጠጋል፤ ሀጀሩን በቀኝ እጁ ይነካዋል፤ ከተቻለው ይስመዋል፤ ካልተቻለው በእጁ ነክቶት ከሆነ እጁን ይስማል፤ በእጅ መንካት ካልቻለ ወደ ሃጀሩ ፊቱን ካዞረ ቡኋላ በእጁ እያመላከተ ተክቢራ ያደርጋል፤ እጁን ግን አይስምም፤ ሰዎችን አለመጋፋቱ እና አለማስቸገሩ ለሱ በላጭ ይሆንለታል።

- ሀጀሩን በሚነካበት ጊዜ፡ ”ቢስሚላህ ወላሁ አክበር” (በአላህ ስም፤ አላህ ታላቅ ነው) ይላል።

- ከዛም ቀኙን ይይዛል፤ ካዕባን በግራው በኩል ያደርጋል፤ ወደ ሩክን አልየማኒ (በየመን ሚያቅጣጨው ማዕዘን) ሲደርስ ሳይስመው ይነካዋል፤ ወደ እሱም አይጠቁምም፤ ተክቢራም አያደርግም፤ ለሱ በሎ ሰዎችንም አይጋፋም። በሁለቱ ማዕዘን (በሩክነል የማኒ እና በሐጀረል አሰወድ) መካከል ሲሆን ከአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላም እና ውዳሴ በሳቸው ላይ ይሁን) የተገኘውን ይህን ዱዓእ

ይላል፡- ረበና አቲና ፊዱንያ ሃሰነተን፣ ወፊል ኣኺረቲ ሃሰነተን፣ ወቂና ዓዛበናር። ፈጌታችን ሆይ! በምድረ ዓለም ደግን ነገር (ጸጋን) በመጨረሻይቱም አገር ደግን ነገር (ገነትን) ስጠን፤ የእሳትንም ቅጣት ጠብቀን} [አልበቀራህ፡ 201].

- ኢድጢባዕ ጠዋፉ ከጀመረበት እስከሚጨርስበት ይሆናል። የኢድጢባዕ ሁኔታውም፡- የቀኝ ትከሻን መግለጽ ነው። ጠዋፉን እንደጨረሰ ትከሻውን ይሸፍናል።
- ረመል በመጀመሪያዎቹ ሶስት ዙሮች ብቻ ይሆናል። ረምል ማለት፡- ፈጠን ባለ እርምጃ ኮቴውን ማከታተል ነው።
- የጠዋፉን ሰባት ዙር ካጠናቀቀ ቡኃላ፤ ከተመቸው ወደ መቃም ኢብራሂም(የኢብራሂም ዓለይሂሰላም የቆሙበት ቦታ) ላይ በመቆም ሁለት ረክዓ ይሰግዳል፤ በመጀመሪያው ረከዓ ላይ ፋቲሃ እና ሱረቱል ካፊሩን በሁለተኛው ረከዓ ላይ ፋቲሃ እና ሱረቱል ኢኽላስ ይቀራል።
- ከዛም ሰግዶ እንደጨረሰ ከቻለ የዘምዝም ውሃ መጠጣት ይወደድለታል። ከቻለ ወደ ሃጀረል አስወድ ይሄድና ሰላም ይለዋል።
- ከዛም ወደ ሰፋ ተራራ ይወጣል፤ ይህንንም ይቀራል፡- ኢነስሰፋ ወልመርወተ ሚን ሸዓኢሪላህ ፈመን ሃጀል በይተ አዊዕተመረ ፈላ ጁናሃ ዓለይሂ አንየጠወፈ ቢሂማ ወመን ተጠወዓ ኸይረን ፈኢነላሃ ሻኪሩን ዓሊም። ፈሶፋና መርዋ ከአላህ (ትዕዛዝ መፈጸሚያ) ምልክቶች ናቸው፡፡ ቤቱን (ካዕባን) በሐጅ ወይም በዑምራህ ሥራ የጎበኘ ሰው በሁለቱ (መካከል) በመመላለሱ በርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም፡፡ መልካምንም ሥራ በፈቃደኛነት የሠራ ሰው

(አላህ ይመነዳዋል)፤ አላህ አመስጋኝ ዐዋቂ ነውና፡፡} [አለበቀራህ፡ 158]፤ ይህንን አንቀጽ ከሰፋ ተራራ ላይ ከመውጣቱ በፊት ሲቃረብ ያነባል፤ ነገር ግን ይህን በዚህ ቦታ ብቻ እና በመጀመሪያው ዙር መጀመሪያ ላይ ብቻ ያነባል፤ በእያንዳንዱ ዙር ላይ አይደግምም።

- ወደ ካዕባን እስኪመለከት ድረስ ሰፋ ተራራ ላይ ከፍ ካለ ቡኋላ ወደ ካዕባ አቅጣጫ ዞሮ "አልላሁ አክበር" ይላል፤ ከዛም ሁለት እጆቹን ያነሳና አላህን ያመሰግናል ዱዓ ያደርጋል። ከአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላም እና ውዳሴ በሳቸው ላይ ይሁን) እንዲህ የሚል ተገኝቷል፡ «ላኢላሃ ኢልለሏሁ ዋህደሁ ላሸሪከለሁ፣ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲር፣ ላኢላሃ ኢልለላሁ ዋህዳህ፣ አንጀዘ ዋዕደህ፣ ወነሰረ ዐብዳህ፣ ወሐዘመል አህዛበ ዋህዳህ» (ከአላህ ውጭ በሃቅ የሚገዙት ሌላ አምላክ የለም፣አንድ ነው፣ አጋር የለውም፣ ንግስና ለርሱ የተገባ ነው፣ ምስጋናም ለርሱ የተገባ ነው፣ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፣ ከአላህ ውጭ በሀቅ የሚገዙት ሌላ አምላክ የለም፡፣ አንድ ነው፣ ቃልኪዳንን ሞልቷል፣ ባሪያውን ረድቷል፣ የጠላትን ኃይል ብቻውን አንኮታኩቷል፡፡) ይህንን ዚክር ሦስት ጊዜ ይደጋግማሉ፡ ፡ ከዛም የፈለገውን ዱዓ ማድረግ ይችላል።

- ከዚያም ከሰፋ ወርዶ ወደ መርዋ ይሄዳል፣ በተለምዶ በሚራመድበት መልኩ እየሄደ አላህን ያወሳል፣ እንዲሁም ለራሱ፣ ለቤተሰቦቹ፣ እና ለወደዳቸው ሰዎች የሚቻለውን ዱዓእ ያደርጋል። አረንጓዴው ምልክት መጀመሪያ ጋር እንደደረሰ፣ እስከ መጨረሻው አረንጓዴ ምልክት ድረስ በተቻለው መጠን ፈጣን ሩጫ ይሮጣል፣ ከዚያም ወደ መደበኛ አረማመዱ ይመለሳል፣ እና ወደ መርዋ እስኪወጣ

ድረስ መሄዱን ይቀጥላል። መርዋ ላይ ሲደርስወደ ቂብላ ፊቱን አድርጎ፣ በሰፋ ላይ እንዳለው ተመሳሳይ ነገር ይላል።

- ከዛም ከሰፋ ወደ  መርዋ የመጀመሪያ ዙር፤ ከመርዋ ወደ ሰፍ ሁለተኛ ዙር፤ እያለ ሰባት ዙር ይመላለሳል። አረንጓዴ ምልክት ያለበት ጋር ሲደርስ ፈጠን ያለ ሩጫን ይሮጣል።በዙሪያ ያሉትን ማስቸገር የለበትም። በዚህ መልክ ሰባት ዙሩን ተመላልሶ ይጨርሳል።
- ከዚያም የጭንቀላቱን ፀጉር ይላጨዋል ወይም ይቀንሰዋል። ሴት ልጅ ደግሞ ፀጉሯን ትሰበስብና የጠቋሚ ጣትን የሚያክል ታሳጥራልች።
- በነዚህም ተግባራት ዑምራው ይጠናቀቃል።በኢህራም ምክኒያት ክልክል የነበሩ ነገሮች በጠቅላላ ይፈቀድለታል።

የአላህ ሰላም እና ውዳሴ በነብያችን ሙሀመድ ላይ፣ በቤተሰቦቻቸው እና በሁሉም ባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን።

# የተመረጡ ዱዓዎች

አልሏሁመ ለከል ሃምዱ፤ ሃምደን ከሲረን ጠዪበን ሙባረከን ፊሂ፤ ከማ ቱሂቡ ረቡና ወተርዳ፤ ሀምደን ላ የንቀጢዑ ወላ የቢዱ፤ ወላ የፍና፤ ሚልአ ሰማዋቲከ፤ ወሚልአ አርዲከ፤ ወሚልኣ ማ ሺእተ ሚን ሸይኢን በዕድ፤ ዓደደ ማ ሀመደከል ሃሚዱን፤ ወዓደደ ማ ገፈለ ዓን ዚክሪከል ጋፈሉን፤ ወሰላቱ ወሰላሙ ዓላ ዓብዲከ ወረሱሊከ ሙሀመድ፤ ኻተሙ አንቢያኢከ ወሩሱሊከ፤ ወኺይረቲከ ሚን ኸልቂከ፤ ወአሚኑከ ዓላ ወህዪከ፤ ወዓላ ኣሊሂ ወስህቢሂ አጅመዒን።

አልሏሁመ ለከል ሃምዱ፤ አንተ ኑሩ ሰማዋቲ ወልአርዲ ወመን ፊሂነ፤ ወለከል ሃምድ፤ አንተ ቀዩሙ ሰማዋቲ ወልአርዲ ወመን ፊሂነ፤ ወለከል ሃምድ፤ አንተል ሃቅ፤ ወወዕዱከ ሃቅ፤ ወቀውሉከ ሃቅ፤ ወሊቃኡከ ሃቅ፤ ወልጀነቱ ሃቅ፤ ወናሩ ሃቅ፤ ወስሳዓቱ ሃቅ፤ ወንነቢዩነ ሃቅ፤ ወሙሀመዱን ሰለላሁዓለይሂ ወሰለመ ሃቅ።

አልሏሁመ ለከ አስለምቱ፤ ወዐለይከ ተወከልቱ፤ ወቢከ አመንቱ ወኢለይ አነብቱ፤ ወቢከ ኻሰምቱ፤ ወኢለይ ሐከምቱ፤ ፊግፊርሊ ማ ቀደምቱ፤ ወማ አኸርቱ፤ ወማ አስረርቱ፤ ወማ አእለንቱ፤ አንተል ሙቀዲሙ ወአንተል ሙአኺሩ፤ ላኢላሃ ኢልላ አንተ፤ ወላ ሀውላ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላሂ አል ዓሊዩል አዚም።

አልላሁመ አቲ ነፍሲ ተቅዋሃ፤ ወዘኪሀ አንተ ኸይሩ መን ዘካሃ፤ አንተ ወሊዩሃ ወመውላሃ።

አልላሁመ ኢንኒ አኡዙ ቢከ ምን ኢልሚን ላየንፈዕ፤ ወሚን ቀልቢ ላ የኽሸዕ፤ ወሚን ነፍሲን ላ ተሽበዕ፤ ወሚን ደዕወቲን ላ ዩስተጃቡ ለሃ።

አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከ ቢአነ ለከል ሃምዱ፤ ላ ኢላሃ ኢላ አንተ፤ በዲዑ ሰማዋቲ ወላርዲ፤ ያዘልጀላሊ ወልኢክራም፤ ያሃዩ ያቀዩም፤ አንተግፊረኒ ወተርሃመኒ፤ ወኢዛ አረትተ ቢቀውሚን ፊትነተን ፈቅቢድኒ ኢለይከ ገይረ መፍቱን።

ረበና አቲና ፊዱኒያ ሃሰነተን፣ ወፊል ኣኺረቲ ሃሰነተን፣ ወቂና ዓዛበናር።

ረበና ኣመና ፈግፊር ለና ወርሃምና፣ ወአንተ ኸይሩ አርራሂሚን።

ረበና ላ ቱዚግ ቁሉበና በዕደ ኢዝ ሃደይተና ወሃብ ለና ሚንለዱንከ ራህመተን ኢነከ አንተል ወሃብ።

ረበና ላ ቱኣኺዝና ኢንነሲና አው አኽጠእና፣ ረበና ወላ ተህሚል ዐለይና ኢስረን ከማ ሀመልተሁ አለልለዚነ ሚን ቀብሊና፣ ረበና ወላ ቱሀምሚልና ማላ ጣቀተ ለና ቢህ፣ ወዕፉ ዐና ወግፊር ለና ወርሃምና፣ አንተ መውላና ፈንሱርና ዐለል ቀውሚል ካፊሪን።

ረቢ ኢጅዓልኒ ሙቂመ አስሰላቲ ወሚን ዙሪየቲ ረበና ወተቀበል ዱዓእ፣ ረበና ኢግፊርሊ ወሊዋሊደየ ወሊልሙእሚኒነ የውመ የቁሙል ሂሳብ።

ረበና ሃብ ለና ሚን አዝዋጂና ወዙሪያቲና ቁረተ አዕዩኒን ወጅዓልና ሊልሙተቂነ ኢማማ።

ረበና አቲና ሚንለዱንከ ረህመተን ወሃዩእ ለና ሚን አምሪና ረሸዳ።

ረበና አቲና ማ ዋዐትተና አላ ሩሱሊከ ወላ ቱኽዚና የውመል ቂያመቲ፤ ኢንነከ ላ ቱኽሊፉል ሚዓድ።

አልላሁመ ኢኒ አስአሉከል ሁዳ ወትቱቃ ወልአፋፈ ወልጊና፡፡

አልላሁመቅሲም ለና ሚን ኸሽየቲከ ማ ተሁሉ ቢሂ በይነና ወበይነ ማዕሲየቲከ፤ ወሚን ጣዐቲከ ማቱበሊጉኒ ቢሂ ጀነተከ፤ ወሚነል የቂኒ ማቱህዊኑ ቢሂ አለየ መሳኢቢዱንያ፤ ወመቲዕ ቢሰመዒ፤ ወበሰሪ፤ ወቁወቲ፤ አበደን ማ አብቀይተኒ፤ ወጅአልሁል ዋሪሰ ሚኒ፤ ወጅአል ሰእሪ ዓላ መን ዘለመኒ፤ ወንሱርኒ ዓላ መን አዳኒ፤ ወላ ተጅዓል ሙሲበቲ ፊ ዲኒ፤ ወላ ተጅዓሊ ዱኒያ አክበረ ሃሚ፤ ወላ መብለገ ዒልሚ፤ ወላ ኢለ ናሪ መሲሪ ወጅአሊል ጀነተ ሂየ ዳሪ፤ ወላ ቱሰሊጥ ዓለየ ቢዙኑቢ መን ላየኻፉከ፤ ወላ የርሃሙኒ፤ በራህመቲከ ያ አረሃመራሂሚን፡፡

አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢዒዘቲከ -ላ ኢላሃ ኢላ አንተ- አንቱዲለኒ፣ አንተል ሃዩ አልለዚ ላ የሙቱ፣ ወልጂኑ ወልኢንሱ የሙቱነ።

አልሏሁመ ፋጢረ ሰማዋቲ ወል አርድ ዓሊመል ገይቢ ወሸሸሃደህ፣ ላ ኢላሃ ኢልላ አንተ፣ ረብበ ኩልሊ ሸይኢን ወመሊኩህ፣ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ነፍሲ፣ ወሚን ሸርሪ ሸይጧኒ ወሸሪኪሂ፣ ወአን አቅተሪፍ ዐላ ነፍሲ ሱአን አው አጁረሁ ኢላ ሙስሊሚን፡፡

አልላሁመ አስሊህ ሊ ዲኒ አለዚ ሁወ ኢስመቱ አምሪ ወአስሊህ ሊ ዱንያየ አለቲ ፊሃ መኣሺ ወአስሊህ ሊ ኣኺረቲ አለቲ ፊሃ መ ኣዲ ወጅአሊል ሀያተ ዚያዳተን ሊ ፊኩሊ ኸይር ወጅአሊል መውተ ራሀተን ሊ ሚን ኩሊ ሸር፡፡

አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከል ዓፊያተ ፊድዱንያ ወኣኺራህ፣ አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከል ዐፍወ ወልዓፊየተ ፊ ዲኒ፣ ወዱንያይ፣ ወአህሊ፣ ወማሊ፣ አልላሁመ ኡስቱር ዐውራቲ፣ ወኣሚን ረውዓቲ።

አልላሁመ ኢህፊዝኒ ሚን በይኒ የደየ ወሚን ኸልፊ፣ ወዐን የሚኒ ወዐን ሺማሊ፣ ወሚን ፈውቂ፣ ወአዑዙ ቢዐዘመቲከ አን ኡግታለ ሚን ታህቲ።

አልላሁመ አህሲን ዓቂበቲ ፊል ኡሙሪ ኩሊሃ፣ ወአጂርኒ ሚን ኺዝዪ አድዱንያ፣ ወዐዛቢል ኣኺራሕ።

አላሁመ አዒኒ ዓላ ዚክሪከ፣ ወሹክሪከ፣ ወሁስኒ ዒባደቲከ።

አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ዘዋሊ ኒዕመቲከ፣ ወተሃዉሊ ዓፊየቲከ፣ ወሚን ፊጃአተ ኒቅመቲከ፣ ወሚን ጀሚዒ ሰኽጢከ።

አልላሁመ ኢነከ አፉዉን ቱሂቡል አፍወ ፈዕፉ አኒ፡፡

አልላሁመ ኢኒ አስአሉካ ምነልኸይረ ኩሊሂ ዓጂሊሂ ወኣጂሊሂ ማ አሊምቱ ሚንሁ ወማ ለም አእመል፤ ወአኡዙ ቢከ ሚነሸሪ ኩሊሂ ዓጂሊሂ ወኣጂሊሂ ማ አሊምቱ ሚንሁ ወማለም አእለም፡፡

አልላሁመ ኢኒ አስአሉከ ሚን ኸይር ማሰአለከ ሚንሁ አብዱከ ወነቢዩከ ሙሀመዱን ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ወአኡዙ ቢከ ሚን ሸሪ መስተዓዘ ሚንሁ ዓብዱከ ወነቢዩከ ሙሀመዱን ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም፡፡

አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከል ጀነተ፣ ወማ ቀረበ ኢለይሃ ሚን ቀውሊን አው ዐመል፣ ወአዑዙ ቢከ ሚነ ናሪ ወማ ቀረበ ኢለይሃ ሚን ቀውሊን አው ዐመል።

አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከ ሙጂባተ ራህመቲከ፣ ወዐዛኢመ መግፊረቲከ፣ ወገኒመተ ሚን ኩሊ ቢር፣ ውስሰላመተ ሚን ኩሊ ኢስም፣ ወልፈውዘ ቢልጀነቲ፣ ወንነጃተ ሚነ ናር።

አልላሁመ ጀንኒብኒ ሙንከራቲል አኽላቂ ወልአዕማል፣ ወልአህዋኢ ወልአድዋእ።

አልላሁመ ኢግፊርሊ ዙኑቢ ጀሚዓ፣ ወህዲኒ ሊአህሰኒል አኽላቅ፣ ላ የህዲ ሊአህሰኒሃ ኢላ አንተ፣ ወስሪፍ ዐኒ ሰዪአሃ፣ ላ የስሪፉ ዐኒ ሰዪአሃ ኢላ አንተ።

አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከ ኸሽየተከ ፊልገይቢ ወሸሸሃዳህ፣ ወአስአሉከ ከሊመተል ሃቂ ፊለገደቢ ወርሪዳ፣ ወአስአሉከል ቀስደ ፊልፊቅሪ ወልጊና፣ ወአስአሉከ ነዒመን ላ የንፊድ፣ ወቁረተ ዐይኒን ላ ተንቀጢዒ፣ ወአስአሉከር ሪዳ ባዕደል ቀዳእ፣ ወበርደል ዐይሺ ባዕደል መውት፣ ወለዘተን ነዘሪ ኢላ ወጅሂከል ከሪም፣ ወሸሸውቀ ኢላ ሊቃኢክ፣ ፊ ገይሪ ደራአን ሙዲራህ፣ ወላ ፊትነቲን ሙዲላህ።

አልላሁመ ዘይዩና ቢዚነቲል ኢማን፣ ወጅዐልና ሁዳተን ሙህተዲን፣ ገይረ ዳልሊነ ወላ ሙዲሊን፣ ሲልመን ሊአውሊያኢክ፣ ሃርበን ዐላ አዕዳኢክ፣ ኑሂብቡ ቢሁቢከ መን አህበክ፣ ወኑዓዲ ቢዐዳወቲከ መን ዓዳክ፣ አው ኻለፈክ።

አልላሁመ ኡንቁልኒ ሚን ዙሊል ምዕሲየቲ ኢላ ዒዝዚጥ ጣዐህ፣ ወግኒኒ ቢሃላሊከ ዐን ሃራሚክ፣ ወቢጣዐቲከ ዐን ማዕሲየቲክ፣ ወቢፈድሊከ ዐምመን ሲዋክ፣ ያ ሀይዩ ያ ቀይዩም፣ ያ ዘልጀላሊ ወልኢክራም።

አልላሁመ ኢንኒ አኡዙ ቢከ ሚነልሀሚ ወልሁዝን፤ ወሚነል አጅዚ ወልከሰል፤ ወሚነል ጁብኒ ወልቡኸሊ፤ ወሚነል ማእሰሚ ወልመግረም፤ወሚን ገለበቲ ደይኒ ወቀህሪ ሪጃል፡፡

አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል በረሲ፣ ወልጁኑኒ፣ ወልጁዛሚ፣ ወሚን ሰዩኢል አስቃም።

አልላሁመ ረበ ሰማዋቲ ወልአርዲ፣ ወረበል አርሺል አዚም፣ ረበና ወረበ ኩሊሸይእ፣ ፋሊቀል ሃቢ ወነዋ፣ ሙንዚለ ተውራቲ ወልኢንጂሊ ወልፉርቃን፣ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ኩሊ ዚሸሪን አንተ ኣኺዙን ቢናሲቲየቲህ።

አልላሁመ አንተል አወሉ ፈለይሰ ቀብለከ ሸይእ፣ ወአንተል ኣኺሩ ፈለይሰ በዕደከ ሸይእ፣ ወአንተ ዛሂሩ ፈለይሰ ፈውቀከ ሸይእ፣

ወአንተል ባጢኑ ፈለይሰ ዱነከ ሸይእ፣ ኢቅዲ ዐኒ ደይነ ወአግኒኒ ሚነል ፈቅር።

አልላሁመ አንተ ረቢ ላ ኢላህ ኢላ አንተ፣ ኸለቅትኒ ወአነ ዐብዱከ፣ ወአነ ዐላ ዐህዲከ፣ ወዋዕዲከ መስተጣዕቱ፣ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ማ ሰናዕቱ፣ አቡኡ ለከ ቢኒዕመቲከ ዐለይየ፣ ወአቡኡ ቢዘንቢ፣ ፈግፊር ሊ፣ ፈኢነሁ ላ የግፊሩ ዙኑበ ኢላ አንተ።

አልላሁመ ኢኒ አስአሉከ ፊዕለል ኸይራት፤ ወተርከል ሙንከራት፤ ወሁበል መሳኪን፤ ወአን ተግፊረሊ ወተርሀመኒ፤ ወኢዛ አረተ ቢዒባዲከ ፊትነተን ፈቅቢድኒ ኢለይከ ገይረ መፍቱን፡፡

አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ጀህዲል በላእ፣ ወደረኪ ሸቃእ፣ ወሱኢል ቀዷእ፣ ወሸማተቲል አዕዷእ።

አልላሃሁ ያ ሙቀሊበል ቁሉቢ ሰቢት ቀልቢ ዓላ ዲኒከ፣ አልላሁመ ያ ሙሰሪፈል ቁሉቢ ወልአብሳሪ ሰሪፍ ቀልቢ ዓላ ጣዓቲከ።

አልላሁመ ላ ተደዕ ሊ ዘንበን ኢላ ገፈርተሁ፣ ወላ ሃመን ኢላ ፈረጅተሁ፣ ወላ ደይነን ኢላ ቀደይተሁ፣ ወላ ሃጀተን ሚን ሃዋኢጂ ዱኒያ ወል ኣኺረቲ -ሂየ ለከ ሪደን ወለና ፊሂ ሰላሀ- ኢላ ቀደይተሃ ያ አርሃመራሂሚን።

ረበና ተቀበል ሚና ኢንነከ አንተ አሰስሚዕኡል ዓሊም፤ ወቱብ ዓለይና ኢነከ አንተ አትተዋቡ አርረሂም።

ረበና ኢግፊር ለና ወሊኢኽዋኒና አለዚነ ሰበቁና ቢል ኢማን፣ ወላ ተጅዓል ፊ ቁሉቢና ጊለን ሊለዚነ አመኑ፣ ረበና ኢነከ ረኡፉን ረሂም።

አልላሁም ኢንኒ አብዱከ፣ ኢብኑ አብዲከ፣ ኢብኑ አመቲከ ናሲየቲ ቢየዲከ፣ ማዱን ፊየ ሁክሙከ፣ አድሉን ፊየ ቀዷኡከ፣ አስአሉከ

ቢኩሊ ኢስሚን ሁወ ለከ፣ ሰመይተ ቢሂ ነፍሰከ፣ አው አንዘልተሁ ፊ ኪታቢከ፣ አው አለምተሁ አሀደን ምን ኸልቅከ፣ አዊስተእስርተ ቢሂ ፊ ዒልምል ገይቢ ኢንደከ፣ አንተጅዓለል ቁርኣነል ዓዚመ ረቢዓ ቀልቢ፣ ወኑረ ሰድሪ፣ ወጀላአ ሁዝኒ ወዘሃበ ሀሚ፤ አልሃሁመ አሊምኒ ሚንሁ ማ ጀሂልት፣ ወዘኪርኒ ሚንሁ ማ ነሲት፣ ወርዙቅኒ ቲላወተሁ አናአ ለይሊ ወአጥራፈ ነሃሪ፣ አለል ወጅሂከለዚ ዩርዲከ አኒ፣ ቢራህመቲከ ያ አርሃመራሂሚን፡፡

አልሏሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ዐዛቢ ጀሃነነም፣ ወሚን ዐዛቢል ቀብሪ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ፊትነቲል መሲሐድደጃል፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን ፊትነቲል መህያ ወልመማተ፣ አልሏሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ማእሰሚ ወል መግረም።

አልላሁመ ኢግፊርሊ፣ ወህዲኒ፣ ወርዙቅኒ፣ ወዓፊኒ፣ ወርሃምኒ፣ አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከ ኸይረል መስአለቲ፣ ወኸይረ ዱዓእ፣ ወኸይረ ነጃሂ፣ ወኸይርል አመል፣ ወኸይረ ሰዋብ፣ ወኸይረል ሃያቲ ወኸይረል መማት፣ ወሰቢትኒ፣ ወሰቂል መዋዚኒ፣ ወሀቂቅ ኢማኒ፣ ወርፈዕ ደረጀቲ፣ ወተቀበል ሰላቲ፣ ወግፊር ኸጢአቲ፣ወአስአሉከ ደረጃቲል ኡላ ሚነል ጀነቲ፣ አሚን።

አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከ ፈዋቲሃል ኸይሪ፣ ወኸዋቲመሁ፣ ወጀዋሚዓሁ፣ ወአውወለሁ፣ ወኣኺረሁ፣ ወዛሂረሁ ወባጢነሁ፣ ወደረጃቲል ዑላ ሚነል ጀነቲ፤ አሚን።

አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከ አን ተርፋዓ ዚክሪ፤ ወተደዓ ዊዝሪ፤ ወቱስሊሃ አምሪ፤ ወቱጠሂረ ቀልቢ፣ ወቱሃሲነ ፈርጂ፤ ወቱነዊረ ቀልቢ፣ ወተግፊረሊ ዘንቢ፣ ወአስአሉከ ደረጃቲል ዑላ ሚነል ጀነቲ፣ አሚን።

አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከ አን ቱባሪከ ሊ ፊ ነፍሲ፤ ወፊ ሰምዒ ወበሰሪ፤ ወፊ ኸልቂ፤ ወፊ ኹሉቂ፤ ወፊ አህሊ፤ ወፊ መህያየ፣ ወፊ መማቲ፤ ወፊ አመሊ፤ ወተቀበል ሃሰናቲ፤ ወአስአሉከ አድደረጃተል ዑላ ሚነል ጀነቲ፤ አሚን።

አልላሁመ ኢህፊዝኒ ቢልኢስላሚ ቃኢማ፤ ወህፊዝኒ ቢልኢስላሚ ቃኢዳ፤ ወህፊዝኒ ቢልኢስላሚ ራቂዳ፤ ወላ ቱሽሚት ቢየ ዓዱወን ወላ ሃሲዳ።

አልላሁመ ባዒድ በይኒ ወበይነ ኸጣያየ ከማ ባዐድተ በይነል መሽሪቂ ወል መግሪብ፤ አልላሁመ ነቂኒ ሚን ኸጧያየ ከማ ዩነቃ አስሰውቡል አብየዱ ሚነድደነሲ፤ አልላሁመ ኢግሲልኒ ሚን ኸጧያየ ቢሥሠልጂ ወልማኢ ወልበረዲ፡፡

አልላሁመ አንተል መሊክ፤ ላ ኢላሃ ኢላ አንተ፤ አንተ ረቢ ወአነ ዓብዱከ፤ ዘለምቱ ነፍሲ፤ ወዕተረፍቱ ቢዘንቢ፤ ፈግፊርሊ ዙኑቢ ጀሚዓ፤ ኢነሁ ላ የግፊሩ ዙኑበ ኢላ አንተ፤ ወህዲኒ ሊአህሰኒል አኽላቅ፤ ላ የህዲ ሊአህሰኒሃ ኢላ አንተ፤ ወስሪፍ ዐኒ ሰዩአሃ፤ ላ የስሪፉ አኒ ሰዩአሃ ኢላ አንተ፤ ለበይከ ወሰዕደይክ፤ ወልኸይሩ ኩሉሁ ፊ የደይክ፤ ወሸሽሩ ለይሰ ኢለይክ፤ አና ቢከ ወኢለይክ፤ ተባረክተ፣ ወተዓለይት፤ አስተግፊሩከ፤ ወአቱቡ ኢለይክ።

አልላሁም ኢንኒ አዑዙ ቢከ አን ኡረደ ኢላ አርዘሊል ዑሙር፤ ወአዑዙ ቢከ ሚነል ቀስወቲ ወል ገፍለቲ፤ ወዚለቲ ወል መስከነቲ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚነል ኩፍሪ፣ ወልፉሱቂ፣ ወሺቃቂ፤ ወሱምዓቲ፤ ወርሪያእ።

አልላ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ማ ዐሚልቱ፣ ወሚን ሸሪ ማ ለም አዕመል፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ማ ዐሊምቱ፣ ወሚን ሸሪ ማ አዕለም።

አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ሃድሚ ወተረዲይ፤ ወሚነል ገርቂ፤ ወልሃርቂ፤ ወልሃረም፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን አን የተኸበጠኒ ሸይጣኑ ኢንደል መውት ፤ወአዑዙ ቢከ አንአሙተ ለዲገ፤ ወአዑዙ ቢከ ሚን ጠመዒን የህዲ ኢላ ጠበዕ።

አልላሁመ ኢኒ አስአሉከ አስሰባተ ፊልአምር፤ ወል አዚመተ አላ ሩሽድ፤ ወአስአሉከ ሹክረ ኒእመቲከ፤ ወሁስነ ኢባደቲከ፤ ወአስአሉከ ቀልበን ሰሊመን፤ ወሊሳነን ሳዲቀን፤ ወአስአሉከ ሚን ኸይር ማ ተእለሙ፤ ወአኡዙ ቢከ ሚን ሸር ማ ተእለሙ፤ ወአስተግፊሩከ ሚማ ተዕለም፤ ወአንተ አላሙል ጉዩብ፡፡

አልላሁመ አልሂምኒ ሩሽዲ፤ ወቂኒ ሸረ ነፍሲ፤ ያሃዩ ያቀዩም፤ አልላሁመ ዚድኒ ወላ ተንቁስኒ፤ ወአክሪምኒ ወላ ቱሂንኒ፤ ወኣዕጢኒ ወላ ተህሪምኒ፤ ወኣሲርኒ ወላ ቱእሲር ዓለየ፤ ያዘል ጀላሊ ወልኢክራም።

አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከ ራህመተን ሚን ዒንዲከ፤ ተህዲ ቢሃ ቀልቢ፤ ወተጅመዑ ቢሃ አምሪ፤ ወተሉሙ ቢሃ ሸዕሲይ፤ ወተህፊዙ ቢሃ ጋኢቢ፤ ወተርፊዑ ቢሃ ሻሂዲ፤ ወተብየዱ ቢሃ ወጅሂይ፤ ወቱዘኪይ ቢሃ ዓመሊይ፤ ወቱልሂሙኒ ቢሃ ሩሽዲይ፤ ወተሩዱ ቢሃል ፊተነ ዐኒ፤ወተዕሲሙኒ ቢሃ ሚን ኩሊ ሱእ።

አልላሁመ ኢንኒ አስአሉከ ሲሃተን ፊ ኢማን ፤ወኢማነን ፊ ሁስኒ ኹሉቅ፤ ወነጃሃን የትበዑሁ ፈላህ፤ ወራህመተን ሚንከ፤ ወዓፊየተን ሚንከ፤ ወመግፊረተን ወሪድዋና።

አልላሁመ ኢነከ ተስመዑ ከላሚ፤ ወተራ መካኒ፤ ወተዕለሙ ሲሪ ወዓላኒየቲ፤ ወላ የኽፋ ዓለይከ ሸይዑን ሚን አምሪ፤ ወአነል ባኢሱል ፊቂሩ፤ ወልሙሰተጊሱል ሙስተጂሩ፤ ወልወጂሉል ሙሽፊቁ፤ አልሙቂሩል ሙዕተሪፉ ኢለይከ ቢዘንቢሂ፤ አስአሉከ

መስአለተል ሚስኪን፤ ወአብተሂሉ ኢልይከ ኢብቲሃለል ሙዝኒቢ ዘሊል፤ ወአድዑከ ዱዓአል ኻኢፊ ደሪር፤ ዱዓአ መን ኸደዐት ለከ ረቀበቱህ፤ ወዘለ ለከ ጂስሙህ፤ ወረጊመ ለከ አንፉህ፤ ፈላሁመ ተቀበል ተውበቲ፤ ወግሲል ሃውበቲ፤ ወአጂብ ደዕወቲ፤ ወሰበተ ሁጀቲ፤ ወህዲ ቀልቢ፤ ወሰዲድ ሊሳኒ፤ ወስሉል ሰኺመተ ሰድሪ፤ ያ አርሃመ አልራሂሚን።

ላ ኢላሀ ኢላ አንተ ሱብሃነከ ኢንኒ ኩንቱ ሚነ ዟሊሚን።

ረበና ዓለይከ ተወከልና ወኢለይከ አነብና ወኢለይከል መሲር፣ ረበና ላ ተጅዓልና ፊትነተን ሊለዚነ ከፈሩ፣ ወግፊር ለና ረበና፣ ኢነከ አንተል ዓዚዙል ሃኪም።

ሱብሃነ ረቢከ ረቢል ዒዘቲ ዓማ የሲፉን፣ ወሰላሙን ዓላ ሙርሰሊን፣ ወልሀምዱሊላሂ ረቢል ዓለሚን።

በመጀመሪያም በመጨረሻም ምስጋና ለአላህ ይገባው።

የአላህ ሰላም እና ውዳሴ በነቢያችን ሙሀመድ፣ በቤተሰቦቻቸው እና በጠቅላላ ባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን።

# ማውጫ


የአስተዳደሩ መግቢያ ........ 4

መግቢያ ........ 6

ሚቃቶች እና ኢህራም ........ 8

ማሳሰቢያ ........ 10

የዑምራ ማእዘናት ገዴታዎች እና ሱናዎች ........ 11

የኢህራም ክልከላዎች ........ 13

የኢህራም ክለከላዎች ፊድያ (ቤዛ) ከመከፈል አንፃር በአይነት ሲከፈሉ ........ 15

የዑምራ አፈፃፀም ሁኔታ ........ 17

የተመረጡ ዱዓዎች ........ 22

ማውጫ ........ 32

حرمين

رئاسة الشؤون الدينية

بالمسجد الحرام والمسجد النبوي